በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 209987

ቀን፡-30/03/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኘ

አመልካች ፡- ፌደራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን-ነ/ፈጂ ተስፋዬ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት ተረፈ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪ በአመልካች ኮሚሽን አለአግባብ ከደረጃና ከደመወዝ ዝቅ ተደርጌያለሁ በማለት ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በአስተዳደር ፍርድ ቤት ዘንድ ባቀረቡት ይግባኝ ከንብረት አወጋገድ፣ከሂሳብ አዘጋግ፣ በኦዲት ግኝት ለይ የተሰጠዉን ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ ከማድረግ እና ሥራዎቼን በወቅቱ ከመፈጸም አንጻር የፈጸምኩት ጥፋት ሳይኖር አለአግባብ ከነበርኩበት ሥራ መደብ አንድ ደረጃ ዝቅ አድርጎ መድቦኛል፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰጠኝ የዲሲፕሊን ውሳኔ አግባብ አይደለም ተብሎ ወደ ቀድሞ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ደረጃ -15 ስራ መደብ ላይ እንዲመልሰኝ እንዲሁም በእግድ ምክንያት ያልተከፈለኝን የሐምሌ እና የነሐሴ ወር 2012 ዓ/ም ደመወዝ ብር 20,300.00 አመልካች እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ በኃላፊነት በኮሚሽኑ የተሰጣቸውን ሥራ በተገቢው አልሰሩም፡፡ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን በተገቢው ጊዜ እንዲያስወግዱ የተጣለባቸዉን ኃላፊነታቸውን በአግባብ አልተወጡም፡፡የኮሚሽኑ የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ እንዲዘጋ በተሰጠው መመሪያ መሰረት በተሰጠው ጊዜ አልተጠናቀቀም፡፡ እንዲሁም የ2013 ዓመታዊ የግዥ ጨረታ ሂደት እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ተጠናቆ ከሐምሌ 01 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ መመሪያ ተሰጥቷቸዉ የነበረ ቢሆንም ተግባራዊ አላደረጉም፡፡ ይህንን በማስረጃ በማረጋገጥ በፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከ2008ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን በጠቅላይ ሚኒስቴሩ በጸደቀዉና በተሻሻለዉ የኮሚሽኑ ሠራተኞችና የሥራ መሪዎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 75(2/5 እና 31) መሰረት ተጠሪ በሥራ መሪነት እንዲቀጥሉ የሚያስችል እምነት አመልካች በተጠሪ ላይ ስለሌለዉ ወደ ሥራ መደቤ ልመለስ ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ሊሰጠዉ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በይ/መ/ቁ 110/13 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 12/04/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ የመንግስት ሠራተኛው በፈፀመው የዲሲፕሊን ጉድለት ተፀፅቶ በአመለካከቱና በሥነ ምግባሩ እንዲታረምና ብቁ ሠራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ተቋም ውስጥ በቆዩባቸው ጊዜያት የፈፀሙት የዲሲፕሊን ግድፈት እንደሌለ የዲሲፕሊን ኮሚቴው የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንን እንደማቅለያ ምክንያት በመቀበል የስር የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 81/3 መሰረት በማሻሻል ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 69(1/መ) መሰረት በአንድ ወር ደመወዝ ተቀጥተዉ የሐምሌ እና የነሐሴ ወራት 2012 ዓ/ም ደመወዝ ክፍሏቸዉ ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንዲመልሳቸዉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ችሎቱ በመ/ቁጥር 202851 ላይ በቀን 11/10/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በጉዳዩ ላይ አመልካች የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ሆኖ እያለ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በይግባኝ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን ሳይኖረው ተመልክቶ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ከሆነ ይሄንኑ ቅሬታውን በቀጥታ ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ በዚህ አግባብ ስህተቱ እንዲታረም ሊያደርግ ከሚችል በቀር ይህ መደበኛ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን የለውም በሚል ምክንያት የይግባኙን ተጠሪን ሳይጠራ ሠርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 21/10/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡ አመልካች ኮሚሽን ሰራተኞችን የሚያስተዳድረው በፌዴረላ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 መሰረት ሳይሆን የኮሚሽኑን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 አንቀጽ 15ን ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 1/2008 መሰረት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2(1/ሠ) መሰረት አዋጁ በኮሚሽኑ ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡በዚህ ደንብ በአንቀጽ 82/3 በማናቸውም ስራ ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ኮሚሽኑ መሆኑን ተመልክቷል፡፡

ስለዚህ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 መሰረት ጉዳዩን ተመልክቶ ያለሥልጣኑ የሰጠዉን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት እንዲያርም ያቀረብነዉን ይግባኝ በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይ ነዉ በሚል ስለሰረዘብን ችሎቱ ተመልክቶ የአስተዳደር ፍርድ ቤት የሠጠዉን ዉሳኔ እንዲሽርልን በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 03/02/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ የሥር የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያስችል ሥልጣን በሕግ ስለተሰጠዉ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሊሆን ይገባል የሚልና ሥረ ነገሩን የሚመለከት መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አከራካሪ የሆነው የአመልካች ኮሚሽነር በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታይ ይችላል ነዉ ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡ በአመልካች ኮሚሽነር የተሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ በተጠሪ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ሊቀርብ አይችልም በማለት አመልካች የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው ገልጾ የተከራከረ ስለመሆኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም፡፡ ሆኖም የዐስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በይግባኝ ተቀብሎ ለመዳኘት የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር1064/2010 መሰረት ሥልጣን እንዳለዉ በመቁጠር በዋናው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ እንደሰጠ ከዉሳኔዉ መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለውም በሚል ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለውም ከተባለ እኔም ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሠርዞበታል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 81 ላይ እንደተደነገገዉ በአስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የሕግ ስህተት ካለ መርምሮ ስህተቱን ማረም እንዲችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ስልጣን ባለው ጉዳይ ላይም ይሁን ስልጣን በሌለው ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የመመልከት ስልጣን እንደተሰጠው ነው፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የመዳኘት ስልጣን የተሰጠውን ጉዳይ ብቻ መርምሮ መወሰን

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

እንዳለበት ከፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በአዋጁ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ወይም በሌላ ሕግ ለሌላ የዳኝነት ነክ አካል የተሰጠን ጉዳይ ተቀብሎ የሚወስን ከሆነ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከስልጣኑ ውጪ የሰጠውን ውሳኔ ማረም የሚችለው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በይግባኝ አይቶ ስህተቱን ለማረም ስልጣን የተሰጠው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሲመረምር አስቀድሞ ሊመረምር የሚገባው ጉዳይም ቅሬታ ባይቀርብበት እንኳን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ሲሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት በሌለው ስልጣን የሰጠው ውሳኔ ከሆነ የስር ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንደሌለው የሚደነግገውን ሕግ እና የፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9 እና 231/1/ለን በመጣስ የሚሰጥ ዉሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ ስለሚሆን ነዉ፡፡ ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት ካለ በይግባኝ የማረም ስልጣን እስከተሰጠው ድረስ የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ተቀብሎ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያስችል ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን መመርመር ነበረበት፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ስልጣን የለኝም ያለበት ምክንያት አመልካች የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ ነው በሚል ያቀረበውን ክርክር መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ ነው አይደለም? የመጨረሻ ነው ተብሎ ተደንግጎ ከሆነም ይህ ማለት የይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም ለማለት የተደነገገ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለው አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ መመርመር የሚገባዉ የሕግ ጭብጥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ላይ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ከስልጣኑ ውጪ በይግባኝ አይቶ ከሆነ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በሌለው ስልጣን ውሳኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት ስለሚሆን ይህ ስህተት መታረም ያለበት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም ነው፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን አለው ወይም የለውም የሚለው በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እስካልሰጠበት ድረስ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ስለማይሆን አመልካች በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ በቀጥታ የሰበር አቤቱታ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

ሲጠቃለል የፌደራል መንግስት ሰራተኞች ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት በሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ላይ የሕግ ስህተት ካለ በይግባኝ የማረም ስልጣን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሆኖ እያለ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት በአመልካች ኮሚሽነር የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ሥልጣን የለዉም በሚል የቀረበለትን ይግባኝ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በይግባኝ የማየት ሥልጣን የለኝም ማለቱ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 81 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 202851 ላይ በቀን 11/10/2013ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ የመዳኘት ስልጣን አለው ብለናል፡፡

3. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገቡን አንቀሳቅሶ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት በአመልካች ኮሚሽነር የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ለማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን መርምሮ ያስቀርባል የሚል ከሆነ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አድርጎ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም